# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕ
ቆብ ወንድም ይሁዳ፤
ለተጠሩት፣ በእግዚአብሔር አብ ለተወ
ደዱትና በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት[ሀ]፤
2ምሕረት፣ ሰላምና ፍቅር ይብዛላችሁ።

## የዐመፀኞች ኀጢአትና የሚጠብቃቸው ፍርድ

3ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው
ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር፤
ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ
ተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር
እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። 4ከረጅም ጊዜ
በፊት ለዚህ ፍርድ[ለ] የተጻፉ አንዳንድ ሰዎች
ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤ እነርሱ
ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣ የአምላካች
ንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡና እርሱ ብቻ
ልዑል ገዣችንና ጌታችን የሆነውን ኢየ
ሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው።
5ምንም እንኳ አስቀድማችሁ ይህን ሁሉ
የምታውቁ ቢሆንም፣ ጌታ[ሐ] ሕዝቡን ከግ
ብፅ ምድር እንዴት እንዳወጣ፣ በኋላ ግን
ያላመኑትን እንዳጠፋ ላስታውሳችሁ እወዳ
ለሁ። 6የሥልጣን ስፍራቸውን ያልጠበቁ
ትን ነገር ግን መኖሪያቸውን የተዉትን
መላእክት በዘላለም እስራት እስከ ታላቁ
ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ ጠብቆአቸ
ዋል። 7እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣ በዙሪያ
ቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኛነትና ከተፈጥሮ
ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ ራሳቸውን
አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም በዘላለም እሳት
በመቀጣት ለሚሠቃዩት ምሳሌ ሆነዋል።
8በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሕልም አላሚዎች
የገዛ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ ሥልጣንን ይቃ
ወማሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም ፍጥረታት
ይሳደባሉ። 9የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካ
ኤል እንኳ ስለ ሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር
በተከራከረ ጊዜ፣ "ጌታ ይገሥጽህ" አለው
እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊከሰው አል
ደፈረም። 10እነዚህ ሰዎች ግን የማያውቁትን
ነገር ሁሉ ይሳደባሉ፤ አእምሮ እንደሌላቸው
እንስሳት በደመ ነፍስ በሚያወቁት ነገር
ይጠፋሉ።
11ወዮላቸው! በቃየን መንገድ ሄደዋል፤
ለገንዘብ ሲስገበገቡ በበለዓም ስሕተት ውስጥ
ወድቀዋል፤ በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋል።
12እነዚህ ሰዎች በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ያለ አንዳች ኀፍረት ከእናንተ ጋር ቀርበው
የሚበሉ ነውረኞች ናቸው፤ ደግሞም ራሳ
ቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች ናቸው፤
እነርሱም በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው
ደመናዎች ናቸው፤ በመከር ወራት ፍሬ የማይገ
ኙባቸው ከሥራቸው ተነቅለው ሁለት ጊዜ
የሞቱ ዛፎች ናቸው። 13የነውራቸውን አረፋ
የሚደፍቁ የተቈጡ የባሕር ማዕበል፣ ድቅ
ድቅ ጨለማ ለዘላለም የሚጠብቃቸው
ተንከራታች ከዋክብት ናቸው።
14ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ተንብዮአል፤
"እነሆ፤ ጌታ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳኑ ጋር
ይመጣል፤ 15ይህም፣ በሰው ሁሉ ላይ ለመ
ፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችን ሁሉ በክፉት
መንገድ በሠሩት የዐመፅ ሥራና በክፉት
በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩት የስድብ ቃል
ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ ነው"።
16እነዚህ ሰዎች የሚያጕረመርሙና ሌሎ
ችን ሰዎች የሚከሱ ናቸው፤ ርኩስ ምኞታ
ቸውን ይከተላሉ፤ በራሳቸው ይታበያሉ፤
ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሌሎችን ይክባሉ።

## ጸንቶ ስለ መቆም የቀረበ ጥሪ

17ነገር ግን ወዳጆች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው
የተናገሩትን አስታውሱ። 18እነርሱም፣ "በመ
ጨረሻው ዘመን ርኩስ ምኞታቸውን የሚከ
ተሉ ዘባቾች ይመጣሉ" ብለዋችኋል። 19እነ
ዚህ ሰዎች በመካከላችሁ መለያየትን የሚፈ
ጥሩ፣ በደመ ነፍስ የሚነዱ መንፈስ የሌላ
ቸው ናቸው።
20እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤ እጅግ ቅዱስ
በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤
በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ። 21ወደ ዘላለም ሕይ
ወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን የኢየሱስ
ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ ሳለ፣ በእግ
ዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።
22ተጠራጣሪ ለሆኑት ራሩላቸው፤ 23አንዳ
ንዶችን ከእሳት ነጥቃችሁ አድኗቸው፤
ለሌሎች ደግሞ በርኩስ ሥጋ የተበከለውን
ልብሳቸውን እንኳ እየጠላችሁ በፍርሀት
ምሕረት አሳዩአቸው።

## ቃለ ውዳሴ

24እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀ
ፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ

1፥1 ማቴ13፥55፤ ዮሐ14፥22፤17፥12፤ ሐሥ1፥13፤ሮሜ1፥1፡6፥7
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ገላ 6፥16፤1ጢሞ1፥2
1፥3 ቀኍ20፤ ሐሥ 6፥7፤9፥13፤ 1ቆሮ 10፥14፤ 1ጢሞ6፥12፤ቲቶ1፥4
1፥4 ገላ2፥4፤ ቲቶ1፥16፤2ጴጥ2፥1፤ 1ዮሐ2፥22
1፥5 ዘኍ14፥29፤ ዘዳ 1፥32፤2፥15፤ መዝ 106፥26፤ 1ቆሮ10፥1-5፤ዕብ3፥16፡17፤2ጴጥ1፥12፡13፤3፥1፡2፤ 1ዮሐ2፥20
1፥6 2ጴጥ2፥4፡9
1፥7 ዘዳ29፥23፤ ማቴ10፥15፤25፥41፤ 2ጴጥ3፥7
1፥8 2ጴጥ2፥10
1፥9 ዘዳ34፥6፤ ዳን10፥13፡21፤12፥1፤ ዘካ3፥2፤1ተሰ4፥16፤ ራእ12፥7
1፥10 2ጴጥ2፥12
1፥11 ዘፍ4፥3-8፤ ዘኍ16፥1-3፡31-35፤ ዕብ11፥4፤2ጴጥ2፥15፤ 1ዮሐ3፥12
1፥12 ምሳ25፥14፤ ሕዝ34፥2፡8፡10፤ ማቴ15፥13፤ 1ቆሮ11፥20-22፤ ኤፌ4፥14፤ 2ጴጥ2፥13፡17
1፥13 ኢሳ57፥20፤ ፊል3፥19፤2ጴጥ2፥17
1፥14 ዘፍ5፥18፡21-24፤ዘዳ33፥2፤ ዳን7፥10፤ ዘካ14፥5፤ማቴ16፥27፤ ዕብ12፥22
1፥15 1ጢሞ1፥9፤ 2ጴጥ2፥6-9
1፥16 ቀኍ18፤1ቆሮ 10፥10፤2ጴጥ2፥10፡18
1፥17 ኤፌ4፥11፤ ዕብ2፥3፤2ጴጥ3፥2
1፥18 ቀኍ16፤ 1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ3፥1፤ 2ጴጥ2፥1፤3፥3
1፥19 1ቆሮ2፥14፡15
1፥20 ቀኍ3፤ኤፌ6፥18፤ ቈላ2፥7፤1ተሰ5፥11
1፥21 ማቴ25፥46፤ ቲቶ2፥13፤ዕብ9፥28፤ 2ጴጥ3፥12
1፥23 አሞ4፥11፤ ዘካ3፥2-፤1ቆሮ3፥15፤ ራእ3፥4
1፥24 ሮሜ16፥25፤ 2ቆሮ4፥14፤ቈላ1፥22

[ሀ]1 ወይም *የተጠበቁት* ሊሆን ይችላል
[ለ]4 ወይም *ፍርድ የተወሰነባቸውን ሰዎች*
[ሐ]5 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ኢየሱስ* ይላሉ

ለሚችለው፣ 25እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው
አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ ዘላለ
ምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥል
ጣን ይሁን፤ አሜን።

1፥25 ዮሐ5፥44፤
ሮሜ11፥36፤
1ጢሞ 1፥17፤
ዕብ13፥8